# ብርቱካን ትፈታ!



ብርቱካን ሚደቅሳ የታሰረችዉ በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ስርዓአት እንዲገነባ ፣ ሕግ የበላይ እንዲሆንና የኢትዮጵያ አንድነት እንዲጠበቅ ነዉ ። የብርቱካን ሚደቅሳ መታሰር በኢትዮጵያዉያን ሁሉ ላይ እንደደረሰ ግፍ ተደርጎ የሚቆጠር ነዉ። በወጣትነቷ በእናትነቷና በጧሪነቷ ለአገራችንም ሆነ ለአፍሪካ የተቃዉሞ የፖለቲካ ትግል ብርቅዬ የሆነቸዉን ዳኛ ብርቱካን ሚደቅሳን ለማስፈታት ሁላችንም የየራሳችንን ድርሻ ለማበርከት መነሳት አለብን። አሁን ካልተነሳን መቼ? እኛ ካልተነሳ ማን ?

As Birtukan Mideksa stood against lawlessness and dictatorship and for Freedom, Democracy and Ethiopian Unity, it is high time for all Ethiopians to stand in solidarity with her and her cause. It is high time we mobilize holding hand in hand to secure the release of this great leader. If not us who? If not now when?



**What can you do to secure her release?**

**Call the following numbers and express your concern that she is a prisoner of conscience, detained solely for the peaceful exercise of her right to freedom of expression & association.**

State Department: Ethiopian Desk
(202) 647-6473
State Department: Switch Board
(202) 647-4000
The White House: Switch Board
(202) 456-1414
Senator Barbara Boxer: Washington DC
(202) 224-3553
Senator Dianna Feinstein: Washington DC
(202) 224-3841

በሎስ አንጀለስ የአንድነት የርዳታና ልማት ድርጅት ለዲሞክራሲ

Andinet LA - www.kinijitla.org

# Free Birtukan!



## የሕሊና እሥረኛ

## Prisoner of Conscience



## ብርቱካን ሚደቅሳ የሕግ ባለሞያ

የ34 አመት ወጣት የሆነችዉ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ሃሌ የምትባል የአራት አመት ሴት ልጅ እናት ስትሆን የ74 አመት እናት ጧሪ ናት። በአዲስ አበባ ከተማ ተወልዳ በየካቲት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን ካጠናቀቀች በኋላ ለፍትህ የነበራት ግንዛቤ ከፌተኛ በመሆኑ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ገብታ በሕግ ዲግሪ ተመርቃለች። በፌደራል ፍ/ቤትም ዳኛ ሆና ያገለገልች ሲሆን በዳኝነት ሥራዋ የሕግ የበላይነትን በትክክል ሥራ ላይ በማዋል ረገድ ታዋቂነትንና ተወዳጅነትን አትርፋለች። በዚሁ ወቅት የ3ኛ ችሎት ዳኛ ሆና የቀድሞዉን የመከላከላይ ሚኒስቴር አቶ ስዬ አብርሃን በዋስ እንዲለቀቁ ብይን በመስጠቷ ከፀጥታ ሃይሎች ከፍተኛ እንግልት ደርሶባታል።ሕግ የበላይ መሆን እንዳለበት በሥራዋ ያስመሰከረችው ዳኛ ብርቱካን ከአገዛዙ በሚሰጥ መመሪያ ብያኔ አልስጥም በማለቷ ከዳኝነት ቦታዋ ለመልቀቅ ተገዳለች።

## ብርቱካን ሚደቅሳ
## የመጀመሪያዋ የሴት ኢትዮጵያዊ ፖለቲካ መሪ

በሃገሪቱ ዉስጥ የሕግ የበላይነት በወረቀት ላይ ብቻ የሰፈረ ፣ በተግባር ግን ፍትህ የሌለ መሆኑን የተገነዘበችዉ ብርቱካን የፖለቲካዉ ሥርዓት ካልተሻሻለ የሕግ ሥርዓቱ ከመንግስት ነጻ ሊሆን እንደማይችል አጥብቃ ስላመነች «በሰላማዊ ትግል ለዉጥ ማምጣት ይቻላል» ስትል ፖለቲካዉን በይፋ ተቀላቀለች። ቅንጅት ከተፈጠረ በኋላ የፓርቲዉ ምክትል ሊቀመንበር በመሆን ለፓርቲዉ አሸናፊነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክታለች።አሁን ደግሞ የቅንጅት ራእይ ወራሽ የሆነዉ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ሊቀመንበር ናት። «ሰዉ ያለነጻነቱ ምንድን ነዉ?” ያለችዉ ብርቱካን ሚደቅሳ የኢትዮጵያ ህዝብ ለመብቱና ለነጻነቱ የሚያደርገዉን ሰላምዊ ትግል እየመራች ያለችና መከፈል ያለበትን መሥውዋእትነት ለመክፈል የተዘጋች ቆራጥ ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ መሪ ናት። ወ/ት ብርቱካን በአፊሪካ ብቸኛ የሴት ፖለቲካ መሪ ስትሆን ይህም የጾታ ጭቆና አሁን በበዛባት አህጉር ለሚኖሩ ሴቶች ትልቅ ምሳሌና አርዓያነት ያለው ነዉ።

## ብርቱካን ሚደቅሳ የሕሊና እሥረኛ

የምርጫዉን መጭበርበር ተከትሎ የመጣዉን የሕዝብ ሰላማዊ ተቃዉሞ በኃይል በመጨፍለቅ በመቶዎች የሚቆጠሩ ንጹህ ዜጎች በአደባባይ ተጨፈጨፉ ፣ ከቅንጅት ከፍተኛ አመራር አባላትና ደጋፊዎች ጋር ብርቱካን ሚደቅሳ በጥቅምት ወር 1998 ዓ.ም ለእሥር ተዳረገች። ለሃያ አንድ ወራት በግፍ በቃሊቲ እሥር ቤት ከታሰረች በኋላ በአገር ሽምግልና ባህል በተደረገ የይቀርታ ሥርዓት በነሐሴ ወር 1999 ዓ.ም ተፈታች። የምትመራው ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ስላሰጋቸዉ ታህሳስ 2001 ዓ.ም ከሕግና ከስርዓት ዉጭ በሆነ ወከባ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ቃሊቲ እሥር ቤት ተወስዳ መስኮትና ብርሃን በሌለበት ጠባብ የቆርቆሮ ክፍል ዉስጥ ታስራለች።

## Birtukan Mideksa –The Lawyer

Birtukan Mideksa is a 34 years old mother of a four year old daughter and caring for a 74 years mother. She graduated Yekatit 12 High School and then from Addis Ababa University in LAW. She was a prominent judge and practicing attorney. Therefore, she is familiar with the law of the land. Clearly, she had presided over numerous cases as a judge and also represented many clients diligently as an attorney. One can accurately argue that Judge Birtukan follows the letter of the law strictly, and interprets the law in accordance with the Constitution. Consequently, when one of the most powerful man in Ethiopia, the former Defense Minister Seye Abraha, accused of a bogus corruption charges and appeared before her, despite the relentless coercion and pressure from her superiors to convict him without sufficient evidence, Judge Birtukan did what her oath, her profession, and her position mandates of her-she released the Minister unconditionally and dismissed the charges against him. Judge Birtukan showed courage and stood for truth notwithstanding being sent to prison, terminated from her job, or serious bodily harm, and even credible death threats. She stood for the rule of law.

## Birtukan Mideksa – The first Ethiopian woman political leader

Birtukan knew that political reforms are needed to change the legal system of Ethiopia which is controlled by the ruling party. She decided to be involved in politics became the first vice chairwoman of the CUD (Coalition for Unity and Democracy) in 2005. Two years later in June 2008 she was elected Chairwoman of a newly formed, replacing the former Kinijit (“CUD”), Unity for Democracy and Justice Party (“UDJ”).

## Birtukan Mideksa – The prisoner of Conscience

Opposition parties almost certainly won a majority of seats in parliament during the 2005 elections, but the governing TPLF stopped the ballot counting and then declared itself winner. Peaceful protests such as strikes and demonstrations were declared illegal. Nevertheless, citizens of Addis Ababa peacefully exercised these inalienable human rights that belong to them. They engaged in a peaceful city-wide stay-at-home strike. They tried to organize peaceful (actually mild) demonstrations. The TPLF then killed hundreds, detained thousands and incarcerated opposition leaders including Birtukan Mideksa in November 2005. After intense traditional elders “mediation” Birtukan was released from the notorious Kaliti prison in August 2007. That was not the end for Birtukan. She is again illegally arrested and is currently in prison to serve a life sentence without any court order or due process of law following her recent warrantless arrest.